ክፍል ዘጠኝ
የግንቦት 7 የኤርትራ ጉባኤ

"የውርጋጦች ስብስብ"....

በሰምንተኛው ክፍል ባቀረብነው የግንቦት 7 የኤርትራ ጉባኤ ሪፖርታዥ ላይ የድርጅቱ ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ሲታመበት የቆየው የመጠጥና የአደገኛ ሱስ ተጠቃሚነት በተለይ ደግሞ ኩፉኛ የተጠናወተው የሴሰኝነት በሽታ በተመለከተ እነዚሁ ምንጮቻችን የላኩልንን ሪፖርት ማቅረባችን ይታወሳል፡፡

በዚህ ዘጠኛው ሪፖርታዥ ላይ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ እና እዛው ኤርትራ ውስጥ የሚገኙ ጥቂት አጫፋሪዎቹ በየመድረኩና በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ በአማራው ላይ ያላቸውን ጥላቻና በአማራ ድርጅቶች ላይ የሚስተጋቡትን ዘለፋ በተመለከተ ምንጮቻችን የተረኩልንን ሪፖርት እንደሚከተለው አቅርበናል፡፡....

ቀደም ሲል በቀረበው ክፍል ሁለት የግንቦት 7 ጉባኤ ሪፖርታዥ ላይ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ **"በአማራነት ዙሪያ በአርበኞች ግንቦት 7 ላይ እየተነሳ ያለው አሉባልታ እና ወደ ዘር ያዘነበለ አደረጃጀት ለድርጅቱ ህልውና አደገኛ ሁኔታ እየፈጠረ መሆኑን"** የሚገልፅ ይዘት ያለው ሪፖርት አቅርቦ እንደነበር መግለፃችን ይታወሳል፡፡ ቀደም ሲል የጨፍጫፊው የወያኔ አግአዚ ቅልብ ጦር አዛዥ የነበረው ኮሎኔል አለበል አማረ ወያኔን ከድቶ ኤርትራ ከገባ በኋላ "የአማራ ዲሞክራሲያዊ ሃይል ንቅናቄ" ወይም "አዲሃን" የሚባል ድርጅት በመመስረት ከአማራ ክልል በርካታ ወጣቶችን ከሳሰባሰበ በኋላ ለሻዕቢያና ለግንቦት 7 የቀን ጅቦች አስረክቦ የግል ኑሮውን ለማመቻቸት ወደ አውሮፓ መሄዱ ይታወቃል።

ይህ የአማራ ወጣት ታጋዮችን ያሰባሰበው ድርጅት መሪው ጥሎዋቸው ከኤርትራ ከወጣ በኋላ በሻዕቢያና በዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የተለያየ አይነት ተጽእኖዎች እየተካሄደባቸው ቢሆንም ይህንን ሃይለኛ ግፊት እና ያለባቸውን ከፍተኛ የሆነ የምግብና የተለያየ የአቅርቦት ችግር በመቋቋም ለግንቦት 7 እጃችንን አንስጥም በማለት በሚያስገርም ፅናትና ቁርጠኝነት እስካሁን ድረስ በመንገዳገድ ላይ ናቸው፡፡

ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በአማራ ህዝብና የአማራን ስም ይዞ በተደራጀ ተቃዋሚ ሀይል ላይ ከፍተኛ የሆነ ጥላቻና ስጋት እንዳለው ይታወቃል፡፡ "ባጎረስኩኝ እጄን ተነከስኩኝ" እንዲሉ የግንቦት 7

ምሶሶና ማገር ሆኖ እዚህ ደረጃ ላይ ያደረሰው አማራው መሆኑን ዘንግቶ በአሁኑ ወቅት ከወያኔ በላይ የህልውና ስጋቱ እንደሆነ ኢድርጎ የሚመለከተው የፈረደበት አማራው መሆኑ ያሳዝናል።።

ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ እግሩ ኤርትራ መሬት ከረገጠበት ጊዜ አንስቶ በአማራ ስም ተደራጅተው የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚዎችን በውህደት ሽፋን ህልውናቸውን ለማጥፋት አለያም ከሻዕቢያ ጋር እየተመሳጠረ ከትግል ሜዳው ለማስወገድ ያላሰለሰ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል።። እስካሁን ባደረገው ጥረትም ቢያንስ በአርበኞች ግንባር ላይ የነነጎነው የተንኮል ሴራ የተሳካለት ይመስላል።። "የአማራ ዲሞክራሲያዊ ሃይል ንቅናቄ" የተባለው ድርጅትም በቁጥጥሩ ስር ለማስገባት የተለያየ ጥረት ቢያደርግም በወጣቶቹ ጠንካራ ተቃውሞ ምክንያት እስካሁን ድረስ ያልተሳካላት ቢሆንም እነዚህ ወጣቶች ከዚህ በኋላ የሻዕቢያንና የዶ/ር ብርሃኑ ነጋን የረቀቀ ተንኮልና ተፅእኖ ተቋቁመው ብዙም መዘለቅ እንደማይችሉ ኤርትራ ውስጥ በነበረኝ አጭር ቆይታ ለመታዘብ ችያለሁ።።

ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በምርጫ 97 ዋዜማ ቀስተደመና የሚባል ጥቂት ጓደኞቹን ያቀፈ ቡድን በጥድፊያ በማሰባሰብ ወደ ቅንጅት በመግባት ድርጅቱን እንዴት እንደተቆጣጠረውና መጨረሻ ላይም እንዴት ለህልፈት እንዳበቃው ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚያውቀው አሳዛኝ ታሪክ በመሆኑ ወደ ዝርዝር መግባቱ አንባቢን ማሰልቸት ይሆንብኛል።። ቢያንስ ቀደም ሲል ከፈፀመው ጥፋት ተምሮ ከተጠናወተው ተቃዋሚ ድርጅቶችን በውህደትና በግንባር ፈጠራ ሽፋን የመቆጣጠርና ህልውናቸውን የማጥፋት በሽታው አሁንም ድረስ ሊፈወስ አለመቻሉ ይገርማል።። በተለይ የአማራ ድርጅቶችን ለማጥፋት የሚያደርገው ለየት ያለ እንቅስቃሴ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ሲከታተል ለቆየ እንደኔ አይነት ሰው ዶ/ር ብርሃኑ የትግል ሜዳውን በብቸኝነት ለመቆጣጠር ካለው ፅኑ ፍላጎት የሚመነጭ እንዳልሆነ በሚገባ አውቃለሁ።። ዋናው ምክንያቱ እሱ ነው የሚል እምነት ኖሮኝም አያውቅም።። ጠንካራ የሆነ የአማራ ተቃዋሚ ድርጅት ቢፈጠር ለፀረ-ወያኔ ትግሉ ብርታት እንጂ ጉዳት እንደሌለው ስላጣውም አይደለም።። የሰውየውን ባህርይ እስከማውቀው ድረስ ዋናው ስጋቱ ጠንካራ የሆነ የአማራ ተቃዋሚ ድርጅት ከተፈጠረ ከአማራው ዲያስፖራ የሚያገኘው ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ሊቋረጥብኝ ይችላል የሚል ፍርሃት ስላለው ብቻ ነው።።

ብዙዎቻችን ለሱ ቅርበት የነበረን ሰዎች ዶ/ር ብርሃኑ ከወያኔነት ወደ ተቃዋሚነት ጎራ የተቀላቀለው ትግሉ በንግድ አይን የሚያስገኝለትን ትርፍ በማስላት እንደነበር በሚገባ እናስታውሳለን፡ ሁሌም የሚያስጨንቀው ኪሱ ውስጥ የሚገባው የገንዘብ መጠን እንጂ ፀረ ወያኔ ትግሉ እንዳልሆነ አሳምራን እናውቃለን።። ሻዕቢያም ቢሆን በኤርትራ መሬት ቀርቶ ኢትዮጵያ ውስጥ ፀረ ወያኔ ትግል የሚያካሄድ ጠንካራ የአማራ ድርጅት እንዲፈጠር ፍላጎት እንደሌለው ከኮሎኔል አለበል በፊትም ሆነ ከእርሱ በኋላ ተስፋ ቆርጠው ኤርትራን ጥለው የወጡ የአማራ

ልጆች የመሰከሩት እውነት ነው:: በሻዕቢያና በዶ/ር ብርሃኑ ነጋ መካከል የተፈጠረው እስትራተጂያዊ ዝምድና ከዚህ ፀረ-አማራ ከሆነው የጋራ አቋማቸው የሚመነጭ መሆኑ ሁሉም ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ በተለይ የአማራው ሊሂቅ ሊያውቀው የሚገባው ጉዳይ ነው::

ከላይ እንደገለፅኩት ኮሎኔሉ በሻዕቢያ "ይሁንታ ፈቃድ" ኤርትራን ለቆ ከወጣ በኋላ የአማራ ዲሞክራሲያዊ ሃይል ንቅናቄ የተባለው ድርጅት ባለበት ከፍተኛ ተፅእኖ ስርም ሆኖ በተለያየ ጊዜ ወደ ግዳጅ ለመሰማራት ጥረት ቢያደርግም በዶ/ር በብርሃኑ ነጋ ሴራ እና የሻዕቢያው ሹም ኮሎኔል ፍጹም ከብርሃኑ ነጋ በሚያገኘው ጠቀም ያለ ጉርሻ ምክንያት ድርጅቱ እንደፈለገው ለመንቀሳቀስ እንዳልቻለ ልጆቹ በምሬት ሲናገሩ ሰምቻለሁ:: ይህንን የተረዳው አብዛኛው ወጣት የአዲሃን ታጋይ “ብርሃኑ በሚመራው ድርጅት ውስጥ ከመግባት አንደኛውኑ ወደ ወያኔ እጅ ሰጥቶ መግባት ይሻላል፤ ብርሃኑ ነጋ የትግል መንፈስ የሌለው ከግንቦት 7 ጋር የተቀላቀሉ ሁሉም ድርጅቶችን ያመከነ አስመሳይ ሰው ነው።” በማለት የሚደረግባቸውን ሁሉም አይነት ጫናዎች ተቋቁመው እስከቻሉ ድረስ በራሳቸው ድርጅት መቀጠልን እንደመረጡ ይናገራሉ።

በነበረኝ አጋጣሚ ሁሉ የወጣቶቹን መንፈስ ቀርቤ ከተረዳሁት በኋላ ኤርትራ በተካሄደው በዚህ የግንቦት 7 “ጉባኤ” ላይ ወያኔ ሳይሆን የአማራ ወጣቶችን ያሰባሰበው ይህ ድርጅት ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ በየደቂቃው ስሙ እየተነሳ ሲወገዝ መስማቴ ብዙም አልደነቀኝም:: በዶ/ር ብርሃኑ እና ጀሌዎቹ በተደጋጋሚ በድርጅቱ ላይ ሲነሳ ከነበረው የውግዘት ውርጅብኝ መካከል :-

- ይህ ድርጅት በግንቦት 7 ላይ ከፍተኛ ችግር የሚፈጥር ስለሆነ በሚገባ ታስቦበት ከወዲሁ እልባት ሊሰጠው ይገባል፤
- ከእኛ ጋር አሉ የምንላቸው የአማራ ተወላጆችም ቢሆኑ ምስጢር እያወጡ ለአዴሃን ልጆች አሳልፈው እየሰጡ ነው፣ ሙሉ እምነት የሚጣልባቸው አይደሉም፤ ልባቸው የሸፈተ ነው፣
- ከአርበኞች ግንቦት 7 ጋር ሲታገሉ የነበሩ የአማራ ወጣቶች እየከዱ ከአዴሃን ጋር እየተቀላቀሉ ነው ወዘተ....የሚል እሮሮ ሲያሰሙ እና ክስ ሲያቀርቡ በተደጋጋሚ አዳምጠናል።

ከዶ/ር ብርሃኑ ጀሌዎች መካከል ከሁሉም በጣም የሚገርምና የሚያሳዝን ሃሳብ ያቀረበው ሺባባው የተባለ (የቀድሞ የኢህአፓ አባል የነበረና አሜሪካን በክፍተኛ የወገብ በሽታ ሲሰቃይ ቆይቶ የቀዶ ህክምና ቢደረግለትም ከወገቡ የነበጠ አቅመ ደካማ አዛውንት) ነበር። ዶ/ር ብርሃኑ በሌለበት መድረክ የወጣቶቹ አፅናኝ እንደሆነ የሚነገርለት ይህ ቀትረ ቀላል አዛውንት ያደረገው ንግግር ሁላችንም ያሰደነገጠ በተለይ የአማራ ተወላጆች በግንቦት 7 ላይ የነበራቸውን ተስፋ ተሟጦ እንዲያልቅ ያደረገ ሁኔታ ነበር ።

በጉባኤው ሰለ አዲሃን ሲነሳ ሺባባው ከመቀመጫ ብድግ ብሎ “ክቡር ሊቀመንበር የተወሰነ ሰውና መሳሪያ እንዲሰጠኝ ከተደረገ ይህንን የአማራ ሃይል ነኝ የሚለው የውርጋጦች ስብስብ መደምሰስ እችላለሁ።” ሲል ተናገረ። ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የቀን ቅዠት የሆነበት የአማራው የወጣቶች ስብስብ በዚህ መልኩ በአዛውንቱ መሰደቡ ከልቡ ቢያስደስተውም በሸማግሌው የቀረበው ሃሳብ ከወጣቶቹ የመንፈስ ጥንካሬ ጋር በማገናዘብ እንደማይሆን በሚገባ ስለሚያውቅ የለበጣ ፈገግታውን አሳይቶት ሊያልፍ ሲል ከውጭ የመጡት አንዳንድ የዲያስፖራ አባላት ግን የብርሃኑን ፈገግታ በከፍተኛ ጭብጨባ ለማጀብ ያደረጉት ጥረት ሌላው አሳዛኝ ክስተት ነበር ።

ከስሜታዊነት ወጥቶ በሰከነ መንፈስ ለሚያስብ ማንም ሰው ወገን በወገኑ ያውም የጋራ ጠላት አለን ብሎ በማመን ህይወቱን አሳልፎ ለመስጠት በረሃ በወጣ ሀይል ላይ እንዲህ አይነት የተንኮልና የክፋት መልእክት ማስተላለፍ፣ ይህንንም ደግፎ ማጨብጨብ በአዳራሹ ምን አይነት የአእምሮ ችግር ያለባቸው ሰዎች እንደተሰበሰቡ የሚያሳይ ነበር። እንዲህ አይነት ሰዎች በተሰበሰቡበት አዳራሽ ውስጥ መገኘቱ ራሱ እውነት ለመናገር የሚያሳቅቅና ለከፍተኛ ፀፀት የሚዳርግ ስሜት ውስጥ እንድገባ አድርጎኝ አልፏል።

ዲስኩሩን በቅርበት ሲከታተሉት የነበሩት ትንታጎቹ የአማራ ወጣቶች ሸባባው አለቃውን ለማስደሰት ሲል ያደረገው ባዶ የእብሪትና ድንፋታ ንግግር ለመስማት ስብሰባው እስኪጠናቀቅ ድረስ መጠበቅ አላሰፈሊጋቸውም ነበር። ለካ ዶ/ር ብርሃኑ "እኛ ጋር ያሉ የአማራ ተወላጆችም ቢሆኑ ምስጢራችንን ለአማራው ድርጅት አሳልፈው እየሰጡ ተቸግረናል" በማለት ያቀረበው ቅሬታ ያለምክንያት አልነበረም። በጉባኤው ምን አይነት አጀንዳዎች ተነስተው ማን ምን እንደተናገረ በየደቂቃው ኢንፎርሜሽኑ ይደርሳቸው ነበር። "የውርጋጦች ስብስብ" ተብለው የተሰደቡት እነዚህ የአማራው ትንታጎች ምላሻቸው ምን ሊሆን እንደሚችል ለማየት እድሜ ብቻ ይስጠን እላለሁ።

ይቀጥላል።.....